“በጎቼን ጠብቅ!”

(ረዐይኬ አባግዕየ)

(ዮሐ. ፳ ፣፲፯ ፤ ፳፩ ፋጥ. ፭ ፣፪ አስከ ፱ ይመ.)

በክህነት የጠባቂነት ሥራ
የደረሰውን ስሕተት “ማረሚያ”

በታላቋ ብሪታንያ

የርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን
ቅድስት ማርያም

መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት
ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.
30/07/ 2014

ጥናታዊ ጽሑፍ
፫ኛ አትም

ማውጫ

መግቢያ .....

የበጎች አረኛ በብሉይ ኪዳን..... ምዕራፍ ፩
የበጎች አረኛ በሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ..... ምዕራፍ ፪
የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ ምዕራፍ ፲
የቸር ጠባቂው ርኅራኄ
የቸር ጠባቂው ፍቅር
የቸር ጠባቂው ትሕትና (ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተም ደግሞ አድርጉ)..... ምዕራፍ ፫

በቅዱስ ጴጥሮስ አማካኝነት የተላለፈ “በጎቼን ጠብቅ“ ሥልጣን ..... ምዕራፍ ፬

የበጎች የጠባቂነት ሥራ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ..... ምዕራፍ ፭

ካህናት እና ምእመናን ከገዙት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ወደ ድንኳን..... ምዕራፍ ፮

መልካም አረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል በድንኳን ላይ.....

ማጠቃለያ

መግቢያ

የበጎች ጠባቂ (“ኖላዊ”)

“**አረኛ**” በግእዙ “ኖላዊ” ይባላል። በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከግሪክኛው ፤ ከላቲን ተወስዶ “ፓስተር” ሲባል ትምህርቱ “ፓስተራል ቲዮሎጂ” በአማርኛችን “ትምህርተ አቡነፈስ” ይባላል። የጥበቃው ሥራ “ፓስተራል ኬር”[1] ይባላል። ኖላዊ (በቁሙ አረኛ) ማለት ነው። አረኛ ኃላፊነት ላለባቸው ሁሉ ምሳሌ መሆኑን በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጧል።

በመካከለኛው ምሥራቅ እንደ አኛም አገር አብዛኛው ሕዝብ በእርሻና በከብት እርባታ ሥራ የሚኖር ነበር አሁን ም ነው። በጥንት የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ የበግ ፣ የፍየል ፣ የሌሎችም እንስሳት መንጋዎች በጣም አስፈላጊ ሀብቶች ናቸው። የከብት ጥበቃ ሥራ እጅግ የታወቀ ፤ የተወደደ ፤ የተከበረ ተግባር ነበር። እስከ ቅርብ ዘመን ሀብታም ሰው ሀብቱ የሚለካው በነበሩት ከብቶች ብዛት[2] ነበር።

ቅዱስ ዳዊት የአባቱን በጎች ሲጠብቅ በጎቹን ስለሚወድ ችግር ይገጥመው ነበር። እንዲህ ይላል ፣

> “የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር። ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር።.... ከኋለው ተከትዬ ጉሮሮውን ይዤ አስጥለው ነበር....” (፩ኛ ሳሙ. ፲፯ ፣፴፬)

የአባቱን በጎች የሚጠብቅ በጎቹን የሚወድ አደራ የተጣለበት አረኛ ነበር። ራሱን አሳልፎ እንደሚሰጥ በምሳሌነት ይታያል። መልካሙ አረኛ ስለ በጎቹ ነፍሱን አስከሚሰጥ ድረስ ይጠብቅ ነበር። በጎቼን ጠብቅ የሚል አደራ አለበት እና ነው። የአረኝነት ሥራ ፀሐይና ቁር ድካምም አለው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በነበረበት ዘመን የበጎች ባለቤቶች በጎቻቸውን በአንድ ሰፊ ወይም ለምለም ሰላም ባለበት ቦታ አየመረጡ በጎችን በመጠበቅ ያሠማሩ ነበር። ውሃ ማጠጣት ፤ መንከባከብ የተለመደ ነበር። ማታ ምሽት ሲደርስ ፤ ከአውሬ ከቀበሮ ፣ ከተኩላ ፣ ከድብ እና ከአንበሳ እንዲሁም ከሌባ ለመከላከል የጋራ በረት የሆነ ውስጥ ያስገቡና ተረኛው አረኛ በበሩ ላይ ተኝቶ ሲጠብቅ ያድራል።
በበሩም ላይ ስለሚተኛ ፤ በረኛ ስለሆነ በጎቹን ለመብላት አውሬ ሲመጣ በሩ ላይ ያለውን ከበላ በኋላ ወደ በጎቹ ይገባል ማለት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማስተማር ራሱን “መልካም የበጎች በር” በማለት በመልካም አረኛ ምሳሌ ተናግሮታል። ምእመናኖችን ደግሞ በበጎች መንጋ መስሎ አስተማረ። ዋናው ምሳሌነቱ ግን እርሱን ተከትለው ለሚነሱት ሐዋርያት ካህናት መሪዎች ነበር። በምሳሌነት ራሱን የበጎች ጠባቂ በማለት ከርሱ በመሪነት ለአገልግሎት ለሚነሱት “በጎቼን ጠብቁ” የሚል የአደራነት ሥልጣን ሰጣቸው። አንዱ ምክንያትና ትርጓሜ ይህ ነው።
“መልካም አረኛ **ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል**” የሚለው ቃል ለሁሉም ፤ ለመልካም አረኞች ሁሉ የተሰጠ ቃል ፤ ትእዛዝም ነው (ዮሐ. ፲ ፣፲፩)።
ራሱ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል እንዲህ በማለት አሏል።

> “እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ (ስለበጎቹ ምእመናን) ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። እኔ ያዘዝኳችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ (ዮሐ. ፲፭ ፣፲፪)።”

ቀደም ባለው ጊዜ እንደተጻፈው የክህነት ሥራ በጠባቂነት ፣ በመጋቢነት ፣ በአረኝነት ፣ በአስታራቂነት ፣ በሐኪም የተመሰለ ነው። ማንኛውም ጳጳስና ቄስ ወይም የበጎች የጠባቂነት ሥራ “ሲመተ ክህነት” ሲወስድ “በጎችን ጠብቅ” የሚል ትእዛዝ አደራነት ይቀበላል። የሚነበበው እና የሚጸለየው ዮሐንስ ወንጌል ም. ፲ እና ም. ፳፩ ቁ ፲፭ ያለው ነው። ስለዚህ ጠባቂና ተጠባቂ ተነጣጥለው የማይኖሩ ናቸው። ትምህርትም ያስፈልገዋል። ነገር ግን ካህኑ ተሾሜያለሁ በማለት ኃላፊውን ሥልጣን በመመልከት በደል ቢያደርስ “በጎቼን ጠብቅ” የሚለውን መለኮታዊ አደራነቱን ባለመወጣቱ ያስወቅሰዋል (ማቴ. ፳፭ ፣፴)። የካህን ሕይወት በጥሩ ምሳሌነት አርአያነት መታየት አለበት። (፩ኛጢሞ. ፬ ፣፲፪)።

“መልካም አረኛ በብሉይ ኪዳን ፣ በሐዲስ ኪዳን ፣ በዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ ፣ ለቅዱስ ጴጥሮስ ከዚያም ታላቁ ሐዋርያት (ለሐዋርያት አማር ለተተኩት) ለካህናት እንዴት እንደተላለፈ እና ትርጓሜውን (አሊጎሪካል) በጥቂቱ እናያለን።

መልካም ንባብ!

---

[1] Pastoral care is related to the need to guide, heal, reconcile, and sustain communities, Church Communities. (Blackwell Reader 2000)

[2] (በኢትዮጵያችንም የከብት ሀብት ቆጠራው በቀንድ ነበር) ፤ የአመቤታችን የቅደሰት ማርያም የአናቷ የሐና አያቶች ቴክታ እና በጥሪቃ ከሀብታቸው ብዛት ከበረውና ከለሙ ቀንድ የወርቅ ቀለበት ያደርጉ ነበር ይላል። የከብቱን ብዛት በቀንዳቸው ላይ በሚሰካው በቀለበቱ ቁጥር ይታወቃልና ነው። (ቅዳሴ ማርያም ትርጉም ገጽ 111)

ምዕራፍ ፮

የበጎች አረኛ በብሉይ ኪዳን

የበግ ጠባቂነት ሥራ በብሉይ ኪዳን ሁለት ነገሮችን ይመለከታል።

፮ኛ) = ራሱ እግዚአብሔር እንደ በግ ጠባቂ ሆኖ የእስራኤል ሕዝብ ደግሞ እንደ በጎች ሆነው እና ደሚጠብቃቸውና እንደሚንከባከባቸው ብዙ ጊዜ ተናግሯል። በነቢዩ ሕዝቅኤል ትንቢት እንዲህ ሲል ተገልጧል።

> “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፤ እኔ ራሴ በጎቼን እፈልጋለሁ ፤ በጥንቃቄም እጠብቃቸዋለሁ። የበግ አረኛ የተበተኑትን በጎች መልሶ እንደሚሰበስብና እንደሚጠብቅ እኔም የእስራኤልን ሕዝብ በአንድነት ሰብስቤ በጥንቃቄ እጠብቃቸዋለሁ። ጨለማም በሆነ በዚያ በጥፋት ቀን ከተበተኑበት ቦታ ሁሉ ሰብስቤ አመጣቸዋለሁ። ከባዕዳን አገሮች ሁሉ አወጣቸዋለሁ። በአንድነትም ሰብስቤ ወደ አገራቸው አስገባቸዋለሁ። ወደ እስራኤልም ተራራዎችና ምንጮች አመራቸዋለሁ። ወደ ጥሩ መስክም አሠማርቼ እመግባቸዋለሁ” (ሕዝ. ፴፬ ፣፲፩)።

በባቢሎን በምርኮ የተበተኑትን (585) እስራኤላውያንን እግዚአብሔር ሕዝቡን መልሶ እንደሚሰበስብ ፤ ራሳቸውን የሚወዱት የይሁዳ ነገሥታት ሕዝቡን ችላ ስለሉት ፤ ስለሰቃዩት እና ስለ ናቁት እግዚአብሔር በሕዝቅኤል አድሮ የተናገረው ነው። ገዢዎች የነበሩትም ራሳቸውን በአረኝነት ይመስሉ ነበር (ኤር. ፪ ፣፳ ፤፲ ፣፳፭ ፤፳፫ ፣፴፬)።

እንዲሁም በትንቢተ ኤርምያስ እግዚአብሔር ከ፵ ዓመት ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ፤ የድኅነት ዘመን እንደሚመጣ ይናገር ነበር። መሪዎችንም እግዚአብሔር በኤርምያስ አድሮ ሲወቅስ እንዲህ ይላል።

> የእግዚአብሔር መንጋ የሆነውን ለሚበትኑና ለሚያጠፉ መሪዎች ወዮላቸው!.... “ሕዝቤን እንደሚገባ አልጠበቃችሁም። ይልቁንም አሳደዳችሁ! ፤ በተናችሁ! ፤ ስለዚህ ስለፈጸማችሁት ክፋት እቀጣችኋለሁ (ኤር. ፳፫ ፣፪)።

ኤርምያስ በአምስት የይሁዳ መሪዎች ነገሥታት ዘመናት የኖረ ነው። እውነተኛ ሰብሳቢ መሪ የሚጠበቀው የነገሥታት ንጉሥ “ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር የተባለው” (ሉቃ.፪ ፣፴፪ ፤ ማቴ.፭ ፣፭) እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር አዲስ ኪዳንን እንደሚያደርግ ፤ ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ ነገሥ ስሙ “እግዚአብሔር ጽድቃችን“ እንደሚባል ተነበየ (ኤር. ፴ — ፴፫)።

ቅዱስ ዳዊት ከእስራኤል ነገሥታት (መሪዎች) ሁሉ ታላቅና ተወዳጅ የሆነ መሪ ነበር። በበግ ጠባቂነት የልጅነት ዘመኑን ያሳለፈ ነው። በገናም ይደረድር ነበር ፤ በጸሎት መዝሙሩ ፤

> *“ኖላዊሆሙ ለእስራኤል አፅምእ። ዘይርእዮሙ ከመ አባግዐ ዮሴፍ።”* **ትርጉሙ**
> (የእስራኤል ጠባቂያቸው (አረኛቸው) ሆይ! ስማን (አድምጠን) ፤ ዮሴፍን (እስራኤልን) እንደ በጎች መንጋ የምታሠማራቸው (የምትጠብቃቸው ስማን) አድምጠን (መዝ. ፹፩(፹) ፣፩)።

እንዲሁም በሌላ ስፍራ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ እንዲህ ብሏል።

> *እግዚአብሔር ይሬእየኒ ወአልቦ ዘየኃጥአኒ። ውስተ ብሔር ሥውር ሀየ ያንድረኒ ፤ ወሐበ ማየ ዕረፍት ሐፀነኒ።* ***ትርጉሙ*** እግዚአብሔር አረኛዬ ነው። የሚያሳጣኝም ነገር የለም። በአማረና በለመለመ ስፍራ ያኖረኛል። ጸጥ ወደ አለ ውሃ (ወደ ሰላም) ይመራኛል (መዝ. ፳፪(፳፫) ፣፩)። በማለት እንደ ጸለየ ተገልጧል።

፪ኛ) ሰውን ለማዳን የሚመጣውን መሢሑን በአረኛ በመመሰል ኢሳይያስ እንዲህ ይላል ፤ “መንጋውን እንደ አረኛ ያሠማራል ፤ ጠቦቶቹን በአንድነት ሰብስቦ በእጆቹ አቅፎ ይወስዳቸዋል” (ኢሳ. ፵ ፣፲፩)።

ምዕራፍ ፯

የበጎች አረኝነት በሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ (ትርጓሜ ወንጌል ዮሐ. ፲ ፣፲፩)

ትርጓሜ (አሊጎሪካል)[3] የተወሳሰበን ነገር ወይም ሊረዱት የማይቻለውን ነገር ትርጓሜ ይደረግለታል። ቅዱስ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ስነጽሑፍ ምን ለማለት እንደተፈለገ ሥርዓት ለማስያዝ ሊቃውንቶች አገናዝበው ትርጓሜ እንዲሰጠው ያደርጋሉ። ይህ የመተርጎም ሕግ የተለያየ ዘዴ አለው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን “የላይ ቤት” እና “የታች ቤት” የትርጓሜ ሕጎች አሉ። በምዕራባውያን ትርጓሜ[4] ዘመኑን እየተከተለ ተሰፋፍቷል። ብዙ የቅዱስ መጽሐፍ ትርጓሜ (Bible Commentary) ተዘጋጅቷል።

---

[3] አሊጎሪካል = በአንጾኪያና በአስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በ፪ኛው ምዕተ ዓመት የተጀመረ የአተረጓጎም ትምህርት ነበር። አሊጎሪካል ማለት የተደበቀውን ግልጽ ማድረግ ፤ ቃሉን መተርጎም ማለት ነው። (ምሳሌ ገላትያ. ፬ ፣፳፭ ፤ በሁለቱ ሴቶች በግራና በአጋር በሁሉቱ ኪዳኖች ብሉይና ሐዲስ ተተርጉመዋል ፤ ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፣፩ ሌላም ..... ይህ አሊጎሪካል ለሥዕል ፣ ለቅኔ ስነጽሑፍ ሁሉ ትርጉም የሚሰጥ ዘዴ ነው።

[4] Hermeneutics (Interpretation) = the word drawn from the name of the Greek god Hermes, who is the “messenger of the gods.” Hermeneutics is a mixture of a hermeneutics of faith … What do we mean by “text,” and what do we mean by “reading”?

በትርጓሜው መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋእለ ትምህርቱ እኔ የበጎች ጠባቂ ነኝ ያለበት ምክንያት ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ ባህል በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ አን ድምታ ሲጀምር እንዲህ ይላል።

1ኛ = “*አንሰ መጻእኩ ለኵነኔ ዝንቱ ዓለም*”[5] ብሎ ነበርና ለምሕረትም እንደመጣ ለማጠየቅ።
2ኛ = “*ለዝንቱሰ ኢነአምር*”[6] ብለውት ነበርና ከየትም እንደመጣ ለማጠየቅ።
3ኛ = “*ኄር ኖላዊ*” አይደለም ብለውት ነበረና “*ኄር ኖላዊ*” እንደሆነ ለማጠየቅ።



ወንጌል ዘዮሐንስ።

አርሶተው፡ ግን ኖላዊ የቀባለ አርሱ። አባግዕ የተባሉ አርሳቸው እንደሆኑ አላወቁም።
፯ ወካዕበ ይቤሎሙ፡ እግዚእ ኢ የሱስ አማን አማን እብለክሙ አነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ።
፯ ዳግመኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የበጎች ደጅ እኔ ነኝ አላቸው
፰ ኵሎሙ፡ እለ መጽኡ፡ እምቅ ድሜየ ሠረቅት ወጥሕልያ ኦ ሙንቱ።
፰ ከኔ አስቀድሞ የመጡ ሁሉ የመምሕርነት ሌባ ወንበዴ ና ቸው እንደ ይሁዳ ዘገለላ እ ንደ ቴውዳስ ዘግብጽ።
ወባሕቱ፡ ኢይሰምዓሆሙ፡ አባ ግዕ።
ነገር ግን አባግዕ ምዕመናን አይቀበሏቸውም።
፱ አነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ ዘ በአማን።
፱ ዘበአማን ለማለት ደገመው እ ውነተኛ ደጅ እኔ ነኝ።
ዘዖአ ብእሲ፡ እንተ ኀቤየ ይ ድኅን፡
በኔ በኩል የገባ ማለት በኔ ያ መነ ሰው ከክህደት ይድናል ወይበውእ፡
ወደ ሃይማኖት ይገባል።
ወይወጽእ፡
ሥራ ለመሥራት ይወጣል፡
ወይረክብ ምርአየ፡
መሰማርያም ያገኛል ማለት እ ሳቱን ስለቱን መስቀሉን ያገኛ ል፡ እንድም እኔን አብነት ያ ደረገ፡ ይድኅን፡ ከናዳ፡ ወይበው እ ወደወንጌል፡ ወይወጽእ።
ለማስተማር፡ ወይረክብ ምርዓ የ። ጕባዔን። እንድም መራዕየ ምዕመናንን፡ እንድም እኔን በ ኵር ያደረገ ይድኅን፡ ከፍዳ፡ ወይወጽእ ከፈቃደ ሥጋ ወይ በውእ፡ ወደፈቃደ ነፍስ። ወይረ ክብ፡ ክብረ ሥጋን ክብረ ነፍ ስን ያገኛል መንግሥተ ሰማይ ን ይወርሳል፡
፲ ወሠራቂሰ ኢይመጽእ ዘእንበ ለ ከመ ይሥርቅ ወይጥብሕ ወ ያኅጕል፡
፲ ሌባ ግን ሊጐዳ ነው እንጂ ሊጠቅም ሊያጠፋ ነው እንጂ ሊያለማ አይመጣም፡ እንድም የመምሕርነት ሌባ ወንበዴ ግን ሊጐዳ ነው እንጂ ሊጠቅም ሊያጠፋ ነው እንጂ ሊያለማ አ ይመጣም፡
ወእንሰኒ መጻእኩ ከመ ይር ከቡ ሕይወተ ዘለዓለም።
እኔ ግን የዘላለም ድኅነትን ያ ገኙ ዘንድ ሰው ሆንኩ በመ ምርኀት መጣሁ።
ወፈድፋደ ይርከቡ።
በነፍስ በሥጋ ለማለት ደገመ ው ይበዛላቸው ዘንድ።
፲፩ አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር። ኢሳ ፵ ፲፩ ሕዝ ፴፬ ፲፫።
፲፩ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ።
ወኖላዊሰ ኄር ይሜጡ ነፍሶ ቤዛ አባግኢሁ።
ባለቤት ለበጎቹ ቤዛ ሰውነቱን አሳልፎ ይሰጣል፡
፲፪ ወአግብሰ ዘኢኮነ ኖላዊ ወዘ ኢኮነ አባግዕ ዘዚአሁ ሶበ ይ ሬኢ ተኵላ እንዘ ይመጽእ ይጕይይ ወየኀድጎን ለአባግ ኢሁ ።
፲፪ ዓባግዕ ገንዘቦቹ ያይደሉ ጠባ ቂ ያይደለ ብንደኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ አባግዕን ጥ ሏቸው ይሸሻል ።
ወእምዝ ይመጽእ ወይመስጠን ተኵላ።
ከዚህ በኋላ ተኵላ መጥቶ ይ ነጥቃቸዋል።
ወይዘርምን ለአባግዕ።
በጎችን ይበትናቸዋል።
፲፫ ወአግብሰ ይጕይይ።
፲፫ ብንደኛ ግን ይሸሻል።
እስመ አግብ ውእቱ።
ብንደኛ ነውና።
ወኢያኅዝኖ በእንተ አባግዕ የበጎቹም ጥፋት አያሳዝነውም አንድም ወኖላዊሰ ኄር ብለህ መልስ። እውነተኛ መምር የም ሆን እኔ ለምዕመናን ቤዛ ራ ሴን ለሕማም ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁ። ወአግብሰ፡ምዕመናን ወገኖቹ ያይደሉ ሐሰተኛ መ ምሕር ግን መናፍቅ ጳጳስ አ ላዊ ንጉሥ በተነሣ ጊዜ ይክ ዳል። ወየኀድግ፡ ምዕመናንን አ ሳልፎ ይሰጣቸዋል። እንደ ፎላ ቀሲስ። ወይመሥጠን ይጣላቸ ዋል። ወይዘርምን አገር አስጥ ሎ ይሰዳቸዋል። ወአግብሰ፡ ሐ ሰተኛው መምሕር ግን ይክዳል አስመ ሐሳዊ ውእቱ። ሐሰተ ኛ ነውና። ወኢያኅዝኖ። የም ዕመናን ጥፋት አያሳዝነው ምና ።
፲፬ አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር።
፲፬ ቸር ጠባቂ እውነተኛ መምሕር እኔ ነኝ።
ወአእምር ዘዚአየ መርዔተየ በትጉን አውቃቸዋለሁ ለምዕ መናን እሞትላቸዋለሁ።
ወየአምሩኒ መራዕይየ፡
ያውቁኛል ማለት እኔን አብነ ት አድርገው ምዕመናን መከ ራ ይቀበላሉ።

“*ምእመናን ወገኖቹ ያይደሉ ሐሰኛ መምህር ግን መናፍቅ... ፤ አላዊ ... ፤ በተነሳ ጊዜ ይክዳል።*
ወየኀድግ ፤ ምእመናንን አሳልፎ ይሠጣቸዋል። ወይዘርምን! አገር አስጥሎ ይሰድዳቸዋል።
ወአግብሰ! ሐሰተኛ መምህር ይክዳል። አስመ ሐሳዊ ውእቱ ፤ ሐሰተኛ ነውና።
ወኢያሕዝኖ ፤ የምእመናን ጥፋት አያሳዝነውምና።” (ቁጥር ፲፫) ትርጓሜው ይህ ነው።

---

[5] ትርጉሙ = የሚገኝበት ቦታ ፭ኛ) “ጌታ ኢየሱስ እኔ የማያዩት ሊያዩ ፤ የሚያየዩት ሊታወሩ “*አንሰ መጻእኩ ለኵነኔ ዝንቱ ዓለም*” **ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጥቻለሁ** ፤ አለው” (ዮሐ. ፱ ፣፴፱)። ፮ኛ) “ስለዚህ በምሳሌ አነግራቸዋለሁ ፤ አያዩ አያዩምና ፤ አየሰሙም አይሰሙምና ፤ አያስተውሉምና” (ማቴ ፲፫ ፣፲፫)።

[6] *ይህን የምናውቀው አይደለምን? አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለጸራቢ ፤ ወስማ ለእሙ ማርያም ፤ ወእዋኒሁኒ ያዕቆብ ወዮሳ ፤ ወስምዖን ወይሁዳ* (ማቴ. ፲፫ ፣፶፭) ይሉት ነበር።

የዮሐንስ ወንጌል
ምዕራፍ ፲

ይህ ምዕራፍ ሲጀምር እውነት እውነት እላችኋለሁ በማለት ነው። ይህን ያለበት ምክንያት በምዕራፍ ፱ ቁጥር ፲፮ በአደረገው ተአምር “ሕግን ሻረ“ በማለት ፈሪሳውያን ግማሾቹ ሲያምኑበት ግማሾቹ ተቆጥተው ነበር። አውር የነበረን ሰው ጭቃ አድርጎ ዓይኖቹን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበር። በዚህ የተነሳ ተለያየ ጥያቄ ጠየቁት። ኢየሱስ ክርስቶስም የአረኝነት ምሳሌውን ነገራቸው።

የበግ ጠባቂነት እንደ ንጉሥ ዳዊት የመሪነት ምሳሌ ነው። ከዳዊት በኋላ እግዚአብሔርን የሚከተል ሕዝቡን በጥሩ የሚመራ መሪ (ጠባቂ) አልነበረም። ከላይ እንደተገለጠው ለሕዝቡ ግድ የሌላቸው ነገር ግን ሥልጣን እና ሀብትን የሚፈልጉ ነበሩ። የእስራኤል ሕዝብም ለሁለት ተከፍሎ ግማሹ በምርኮ ሄዶ እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል።

> “እረኞችም በጎቼን ስለለሰማሩ ፤ በጎቼ ንጥቂያ ሆነዋልና ፤ በጎቼም ለምድር አራዊት ሁሉ መብል ሆነዋልና“ ይል ነበር ፤ (ሕዝቅኤል ም. ፴፬)።

ስለዚህም ፈሪሳውያን አንተ ማን ነህ ባሉት ጊዜ “እኔ መልካም እረኛ ነኝ” አላቸው። ይህን ምስጢር ለፈሪሳውያን በምሳሌ ነገራቸው። በትርጓሜው እንደሚታየው ምስጢሩም በሁለት መንገድ በምእመናን መካከል ላለው ግንኙነት ምሳሌ ሆኖ የቀረበ ነው። የሚከተሉትን አማኞቹን በጎች እያለ ሲጠራ ፈሪሳውያንን ቀበሮ እያለ ይጠራቸው ነበር (ማቴ. ፯ ፣፲፭)።

፩ኛ) ትርጉም =

> መልካም እረኛ በጎቹን ለምለም ሣር ወደ አለበት ሥፍራ ፤ የጠራ ውኃ ወደሚገኝበት ወደለምለም ቦታ እንደሚያሠማራቸው ኢየሱስ ክርስቶስም ምእመናንን ቃለ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለሥጋዊ ሕይወት ጭምር የሚያስፈልጋቸውን ምግብና መጠጥ ያሹትን በቸርነቱ ይሰጣል። የምእመናንን ጤንነት በቸርነቱ ይጠብቃል።

ለምእመናን ቸር ጠባቂ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አውቀውና ድምጹን (ቃሉን) ሰምተው የእርሱን ፍለጋ እን ዲከተሉ ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጎችን የሚተናከሉትን ይቃወማል። ስለበጎቹ ይገደዋል።

፪ኛ) ትርጉም =

> “የበጎች ጠባቂነት“ ሥራ በአባግዕ (በበጎች) የተመሰሉ ምእመናንን የሚጠብቁ እረኞች ቸር ጠባቂዎች (“ሮላዊ ጌር”) ፩ኛ) ጳጳሳት ፪ኛ) ቀሳውስት ፫ኛ) መምህራን ናቸው። ይህን “ሮላዊ ጌር” የጠባቂነት ሥርዓት ጌታ ውደ ሐዋርያት ከዚያም ወደ ቤተክርስቲያን መሪዎች “በጎቼን ጠብቁ”[7] ብሎ አስተላለፈ። መንጋው ከእግዚአብሔር በኃላፊነት የተቀበሉት እንጂ የእነርሱ ንብረት አይደለም።

አሊጎሪካል የሚባለው ሥዕለ ክርስቶስ

“እኔ ስለ በጎቼ ራሴን አሳልፌ አሰጣለሁ” ብሏል። በዚህ መሠረት የነፍስ አረኛ ሲሆን ለተከታዮቹ መሪዎች የረኞች አለቃ በመሆኑ መሪ ፣ አስተማሪ ፣ ይባላል ተከታዮቹንም በጴጥሮስ አማካኝነት “በጎቼን ጠብቁ“ ተብለዋል (፩ኛ. ጴጥ. ፪ ፣፳፭)

ይህ ምሳሌ የተወሰደው ቅዱስ ዳዊት ነው። ቅዱስ ዳዊት በእረኝነት በነበረበት ጊዜ በጎቹን ስለሚወድ ተኩላና ቀበሮ ሲመጣ ብዙ ችግር ይገጥመው ነበር (፩ኛ ሳሙ. ፲፯ ፣፴፬)።

---

[7] በምዕራባውያኑ የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። “Feed my lambs.” , “Tend my sheep.” “Feed my sheep.” (NRSV, KJV) “Feed my lambs.” “Take care of my sheep.” “Feed my sheep.” (NIV)

የቸር ጠባቂው ርኅራኄ

ርኅራኄ የክርስትና መሠረት ነው። ከፍተኛ ቦታ የያዘ ከእምነት (ከሃይማኖት) ጋር የሚሄድ ሥራ (ምግባር) ነው። በዘመኑ አጠራር ከክርስትና ውጭ የሆኑት ወገኖች እንኳን ሰብአዊ ርኅራኄ ወይም ሰብአዊ በጎ አድራጎት (Humanity) የሚባለው ይህን ያምናል። መሠረቱም የክርስትና አምነት ነው።

ክርስቲያን ክርስቶስን ከሚመስሉበት እና ከሚከተሉበት ተግባር ዋናው ርኅራኄው ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከርኅራኄው የተነሳ ስለ ሰው ልጆች ሞተ። ሰውንም አዳነ። ሥጋዬን ብሉ ደሜንም ጠጡ ብሎ ለተጠሙት ምግብና መጠጥ አድርጎ ሰጠ። የርኅራኄ ሥራ ሁሉ ሠርቶ አሳየ። እውነተኛ ክርስቲያን ይህን አስተማሪውን ይከተላል። ክርስቲያን ይህን ከተከተለ “በጎቼን ጠብቅ” የተባለው ካህን የበለጠ መሆን ይገባዋል።

ለሎች በጎች ስላሉ አንቺ ገደል ግቢ!። አይልም!

ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ አይፈቅድም (ማቴ. ፲፰ ፥፲፬)

የእውነተኛ ሃይማኖተኛነት ምልክቱ ሰብአዊ ርኅራኄው ነው።
ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ይላል ፤

> “አግዚአብሔር አንድ አንደ ሆነ አንተ ታምናለህ። መልካም ታደርጋለህ ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይን ቀጠቀጡማል። አንተ ከንቱ ሰው ፤ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን?”

ማመንማ አጋንንትም ያምናሉ ፤ ነገር ግን ምግባር (በጎ ሥራ) ርኅራኄ የላቸውም። እንዲሁም ለሰው ልጅ ምቀኞች አጋንንት ናቸው ይላል (ያዕ. ፪ ፥፲፱ ፤ ማር. ፭ ፥፳፪)።

ርኅራኄ የሚፈጸመው አግዚአብሔር አምላክን ከመውደድ ፤ ሕጉን ከመጠበቅ የተነሳ ነው። እንዲሁም ባልንጀራን እንደራስ ከመውደድ የተነሳ ይፈጸማል። ግን ራስን የመውደድ ጠባይ ደግሞ በሰው ባሕርይ ሰፍኖ ይገኛል። በዚህን ጊዜ ርኅራኄ ቦታ የለውም። ፍቅረ አግዚአብሔር (አግዚአብሔርን ማፍቀር) ፤ ፍቅረ ቢጹ (ወንድምን መውደድ) በሰው ልቦና (በበጎ ምኞት) ጎልቶ ከተገኘ ሰብአዊ ርኅራኄም ያለምንም ማመንታት ይፈጸማል። የራሳቸውን ጥቅም ፣ የራሳቸውን ክብር ፣ የራሳቸውን የበላይነት የሚወዱ ከሆነ የበጎች ጠባቂነት ሥራው ይበላሻል።

ርኅሩኁ ቸር ጠባቂ የደከመን ተሸክሞ በአራኣያነት ይታያል

በዚህ ቦታ የክርስቶስ ተከታይ መሪዎች ራሳቸውን የሚወዱ እና የራሳቸውን ዓለም አፍቃሪ ከሆኑ “በጎቼን ጠብቅ” የሚለውን በመተው ያለ ርኅራኄ እኔ ያልኩት ካልሆነ በሚል ምእመናንን የሚያሰቃዩ ከሆነ ያስወቅሳል። በጎች ጠባቂነት ሥራ ታላቅ ኃላፊነት ፤ አደራነት ፤ ከባድነት መሆኑን ሊዘነጉት አይገባም።

የቸር ጠባቂው ፍቅር

የሕግጋቱ ሁሉ መደምደሚያ ፍቅር መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል (ማቴ. ፳፪ ፣፴፯)።

“ወካልእታሂ አንተ ትመሳሰል አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ“ ትርጉም

የመጀመሪያው ትእዛዝ በመሉ ልብህ ፤ በፍጹም ሰውነትህ ፤ በፍጹም ኃይልህ በፍጹም አሳብህ እግዚአብሔርን ውደድ። ሁለተኛዪቱም ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የምትል ናት (ዘሌ. ፲፱ ፣፲፰)።

ለዚህ ፭ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፣፲፫ ማንበብ ጠቃሚ ነው።

ሁሉ ሲያልፍ ፍቅር ብቻ ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር በመሆኑ ሃይማኖትና ተስፋ በዚህ ዓለም አስካለን ድረስ ብቻ ይሠራሉ። ፍቅር ግን ለዘላለም አያቋርጥም (ቁጥ. ፰) ፍቅር ዘላለማዊ ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እን ደመሆኑ ቅዱሳን ጻድቃንም እግዚአብሔርን ተዋሕደው እግዚአብሔርን ለብሰው ፍቅሩ የማይጠገብ ሆኖ ይኖራል።

በፍቅር አማካይነት ወይም ከፍቅር የተነሳ ሕግጋቱ ሁሉ ይፈጸማሉ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል።

ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው (ሮሜ. ፲፫ ፣፲)።

አንድ ልጅ አባቱን የሚያፈቅረው ከፍርሀት የተነሳ አይደለም። ጠንካራና ጽኑእ ፍቅን በሞት እንኳን የማይለወጥ ተላልፎም ለመሞት እንኳን የሚያበቃ ነው። እግዚአብሔር ዓለሙን በጸና ፍቅሩ ስለወደደው ፭ድያ ልጁን ለሕማም ለሞት ሰጠለት (ዮሐ. ፫ ፣፲፮)። እንግዲህ የእውነተኛ ክርስቲያን ፍቅር ስለ እግዚአብሔር ስለ ባልን ጀራውም ቢሆን ተላልፎ እስከ መሞት የሚያደርስ ፍቅር ሊኖረው ይገባል።

ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ ጠፍቶ ስለ ተገኘው አዳም (የሰው ዘር)

ፍቅር ሰሐቦ ለወልደ ኃያል አመንብረ ወአብጽሆ እስከ ለሞት። ትርጉም

“ኃያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው ፤ እስከ ሞትም አደረሰው“ (ቅዳሴ ማ.)

ቅዱስ ወንጌል ቀጥታ የሚለውን እንይ (ማቴ. ፲፰ ፣፲፪)

ቁጥ. ፲፪/ መቶ በጎች ያሉት ሰው ቢኖር ከመካከላቸውም አንዱ ቢጠፋው ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ላይ ትቶ የጠፋውን ሊፈልግ ይሄደ የለምን? ቁጥ. ፲፫/ ባገኘው ጊዜም ካልጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በርሱ ደስ ይለዋል።

ይህን በመጥቀስ “ጠፍቶ ስለ ተገኘው ስለ አዳም ነው እና የፈጣሪን ለፍጡር መስጠት አይገባም“ ሲሉ ዲያቆኑ ደበላልቀው በትችት መልክ ሰበኩ ፤ ቁጥር ፲፬ አልቀጠሱም። ስብከቱን ለማስተካከል!።

ቁጥ. ፲፬/ *እንዲሁም ሰማያዊ አባቴ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ አይፈቅድም* (ማቴ. ፲፰ ፣፲፬)

ትርጓሜው እንዲህ ይላል “እንቀጸ ንሥሐ ነው። አንድም ሲል ደግሞ በሰማያዊ አባቴ ንሥሐ በሚገቡ ሰዎች ደስ ይለዋል። አንዱ ሲጎዳ (*አንዱ እንዲጠፋ*) አይወድም። መቶ በጎች የተባሉ መቶ ነገደ መላእክት ናቸው ከመቶው አንዱ ዲያብሎስ ቢወጣ በሱ ስፍራ አዳም ቢገባ አዳም ቢወጣ ባሕርየ መላእክትን ትቶ ባሕርየ አዳምን ገንዘብ ማድረጉን መናገር ነው። (ትርጓሜ ወንጌል ገጽ 136)

በእርግጥ ትርጓሜው አንድም ተብሎ የሚተረጎም ነው አንጂ አዳም በሚለው የሚቆም አይደለም። አዳም ማለት አንድ ሰው የቀድሞውን ፍጥረት ብቻ ተብሎ አይቆምም። የሰው ዘር ማለት ነው። በተለምዶ በሕዝብ አነጋገር “አዳሜ“ ሲባል እንሰማለን ፤ የጋራ የወል ስም ይሆናል። ስለዚህ የሰው ዘር (አዳም) መሪዎች **የበግ ጠባቂዎች ፍቅር እስከሞት ለተከፈለለት ለሰው ልጅ** ከአውሬው ከሠይጣን ወጥመድ ፤ ከክፉ ነገር መጠበቅ ይገባቸዋል።

ምዕራፍ ፫

የቸር ጠባቂው ትሕትና

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትዕዛዝ ያስተላለፈልን ፤ ስለትሕትና ያሳየው ብዙ ነገር አለ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ለአናንተ አንዳደረግሁ አናንተም ታአደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ (የሐ. ፲፫ ፣፲፫)።

ጌታ ወደ መሰቀል ከመሄዱ በፊት አስቀድሞ በዮሐንስ እንደተጻፈው የጸሎት ቃል የጸለየበት ሌሊት (ጸሎተ ሐሙስ) ወይንም በኦሪት ዘመን ይሠዋ የነበረዉን የኦሪት መሥዋዕት የላሙን ፣ የበጉን ያስቀረበትና በዚህ ፈንታ ሥጋውን ፤ ደሙን የሰጠበት ሌሊት ፤ የሐዋርያቱን እግር ያጠበበት ፤ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ብሎ አዲስ ትእዛዝ የሰጠበት ዕለት ነው።

> አናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ እንዲሁ ነኝና ፤ መልካም ትላላችሁ ፤ እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ አናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለአናንተ አንዳደረግሁ አናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችሁለሁና (ዮሐ. ፲፫ – ፲፭)።



በዚህ በጸሎተ ሐሙስ ሲደርስ የሚደረግ የዓመት ሥርዓት ምስጢሩን ሳይረዱ መሞገቻ አይደለም።

ይህም ትርጉም አለው። ትርጓሜው እንደሚለው ትሕትናን አድርጉ ነው። ከቀድሞ ጀምሮ የተወረሰ ነው። ትሕትና ማለት ራስን ዝቅ ማድረግ ፤ አለመታበይ ፣ ምእመናንን ማክበር ነው። ለክርስቲያን አምነት እና ስነ ምግባር መታወቂያው ትሕትና ነው። ይህ ትሕትና የተመሠረተው በመምህራችን ነው። “በጎቼን ጠብቁ” ፤ **እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ** ፤ “ከኔ ተማሩ እኔ የዋሕ ነኝና ፤ ልቤም ትሑት ነውና”... (ማቴ. ፲፩ ፣፳፱) በማለት ትሕትናን አስተምሯል። ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ትሕትና መሪና አስተማሪነት ብዙ ማለት ይቻላል። ይህን “**የበጎች ጠባቂ**” የበለጠ ሊያደርገው ይገባል። የትሕትና ተቃራኒው ትዕቢት ፣ ኩራት ፣ ሐኬት የመሳሰሉት ... ናቸው። ሽማግሌን መስደብ ፤ ሽማግሌ ላይ ምራቅ... ፤ ዝርጠጣ! ከበጎች ጠባቂ ከሆኑት ሊታይና ሊሰማ አይገባም። የቤተ ክርስቲያን ልጆች ያደጉት *“አስመ በትሕትና ረከበ ልዕልና”* እየተባሉ ነበር። በባህላችንም *“ከማጠቢያ ሁሉ ሳሙና ከሥራ ሁሉ ትሕትና”* ይባላል። ትሕትናና አክብሮት ከሰው ጋር የሚያኖሩ ባሕርያት ናቸው።

ምዕራፍ ፬

ለቅዱስ ጴጥሮስ አማካኝነት የተላለፈው “በጎቼን ጠብቁ” ሥልጣን

ቅዱስ ጴጥሮስ በእርሱም አማካይነት መላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የጠባቂነት ሥልጣን ተሰጥቷል።

> “ስምኦን ወልደ ዮና ታፈቅረኒኑ ፈድፋደ እምእሉ ... ረአይኬ አባግዕየ! ፤ ረአይኬ መሐስዕየ! ፤ አባግዕየ“ የዮና ልጅ ስምኦን ከነዚህ ይበልጥ ትወደኛለህን... “በጎቼን! ጠቦቶቼን! ግልገሎቼን! ጠብቅ“ (የሐ. ፳፩ ፣፲፯)

በመልእክቱ በእረኝነት ተግባር ለተሠማሩት ካህናት ፤ <u>ከእረኞች አለቃ</u> የተሰጠ ትእዛዝ ነው።

መጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት

ምዕራፍ ፭ ቁጥር ፩ — ፭

> አንግዲህ እኔ ከአነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንኩ ፤ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች (ቀሳውስቶች) እመክራቸዋለሁ። በአናንተ ዘንድ ያለውን **የእግዚአብሔር መንጋ ጠብቁ**። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ {በፍቅር} እንጂ በግድ ሳይሆን። በበጎ ፈቃድ እንጂ ፤ መጥፎውን ረብ {የማይረባ ሥልጣን ፣ የራስን ክብር} በመመኘት ሳይሆን ጎብኙት። ለመን ጋው ምሳሌ ሁኑ። እንጂ ግሳበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ። **<u>የእረኞች አለቃ</u>** በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ። እንዲሁም ጎበዞች ሆይ ለሽማግሌዎች ተገዙ። ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ። እግዚአብሔር **ትዕቢተኞችን ይቃወማልና**። ለትሑታን ግን ጸጋን ይሠጣል።

ስለዚህ በቅዱስ ጴጥሮስ አማካኝነት “በጎቼን ጠብቅ”! የተባሉ አረኞች ካህናት የክርስቶስ መንጋ የሆኑት ምእመናንን በነጣቂ አውሬዎች እንዳይወሰዱና እንዳይበሉ በሚገባ እየተንከባከቡ የጠበቁ እንደሆነ ከአረኞች አለቃ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ታላቅ ዋጋና ክብር እንደሚያገኙ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አረጋግጧል።

ቅዱስ ጳውሎስም ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ (የሐዋ. ፳ ፣፳፰)። በማለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መክሯል። አረኞች በጎቻቸው አደጋ እንዳይደርስባቸው በትጋትና በጥንቃቄ የደከሙትን ፣ የታመሙትን ይጠንቀቁላቸው ይላል። (ህመም ማለት የነፍስም የሥጋም ነው)።

ጳጳስ እና ቄስ ወይም የበጎች የጠባቂነት ሥራ “ሲመተ ክህነት” ሲሰጠው “በጎችን ጠብቅ” የሚል ትእዛዝ ነው። የሚነበበው የሚጸለየውም ዮሐንስ ወንጌል ም. ፲ እና ም. ፳፩ ፣፲፯ ፤ ፳፫ጴጥ. ፭ ፣፭ ነው።

በጎቹ ሲጎዱ እየተመለከተ ዝም የሚል አረኛ ካለ ይህ ሰው አደራውን አልጠበቀምና ምንደኛ ወይም ለራሱ ለጥቅሙ ብቻ የሚያስብ ቅጥረኛ ይባላል። ይህ ሰው የጠባቂነቱን አደራነት ከወሰደ በኋላ ባለመወጣቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣቱን እንደሚያገኝ የተረጋገጠ ነው።

እንዲያውም የካህናት ብቻ ሳይሆኑም ክርስቲያኖችም ቢሆኑ ለሌሎች ክርስቲያኖች አረኞች ሆነው በአውሬ እን ዳይነጠቁ መጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ አለባቸው። የመንጋው ኃላፊነት የካህናት ብቻ አይደለም። ኃላፊነቱ የምእመናንም ጭምር ነው።

ምዕራፍ ፭

የበጎች ጠባቂነት ሥራ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ይህ የበጎች ጠባቂነትን ትምህርት ፤ “ትምህርተ አበ ነፍስ” ውይም “ፓስቶራል ቴዮሎጂ ይባላል”።

በመጀመሪያ በአባ ሰላማ (ፍሬምናጦስ) በኢትዮጵያ ወንጌል ሲሰበክ በክርስቲያናዊ ሕይወት አርአያ የሚሆኑትን ቀሳውስት እየመረጠ ምእመናን ካሉበት ሄደው እንዲያስተምሩ ማድረግ ነበር። እነዚህም ወንጌልን ለማስፋር የተሠማሩ ካህናት “የበጎች ጠባቂ” “ኖሎዊ” የሚል ስም ነበራቸው። “አበ ነፍስ” ወይም “አበ ንሥሐ” የሚለው ቃል በኋላ ዘመን የመጣ ነው። በዚያ ጊዜ የነበረው ስያሜ “ኖላዊ” ወይም “አረኛ” የሚል ነበር። ለብዙ ሲሆን “ኖሎት“ ይባላል። “ኖላዊ” ማለት ቀጥተኛ ትርጉሙ “አረኛ” ማለት ነው። አረኛ ማለት ደግሞ አስተዳዳሪ ፣ መሪ ፣ መጋቢ ፣ ጠባቂ ማለት ነው።

ከዮዲት ወይም ከጉዲት በኋላ የተነሱት ቀሳውስት ግን ስያሜው የቤተ እንስሳትን ከሚጠብቀው አረኛ ጋር ስለተመሳሰለባቸው “ኖላዊ“ የሚለውን ቃል “አበ ነፍስ” “አበ ንሥሐ” በሚሉት ቃላት እንዲተካ አደረጉ። (ብሩክ ገብረ ሊባኖስ ገጽ ፭፭)

ከዚህ በመነሳት የበጎች የጠባቂነት ሥራ ለዘመናት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን “የነፍስ አባት“ በአረኛ ምእመናን (በነፍስ ልጆች) ደግሞ በበግ (በመንጋው) ተመስለዋል።

አረኛ ለበጎች እንደሚያስብና እንደሚጨነቅ የነፍስ አባቶችም ለልጆቻቸው ይጨነቃሉ። ሲጨነቁም ኖረዋል። ይህን ኃላፊነት ሥራ ኢትዮጵያውያን ካህናት ሲሠሩ ኖረዋል። ክህነታቸውም የሕዝብ ነው። ሕዝብንም በትሕትና ፣ በቀናነት ፣ በአስታራቂነት ፣ በጠያቂነት እና በአስተማሪነት በሌላም ማኅበራዊ ጉዳዮች እየገቡ ሲሠሩ ኖረዋል። ካህን ጎዳጌ በቀል ነው። ይቅር ባይ ነው። የሕዝብ ነው።

ምዕራፍ ፮

ካህናት እና ምእመናን ከገዙት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ወደ ድንኳን

የለንደን ደብረ ጽዮን ካህናት እና ምእመናን በሰው አገር ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በመግዛት የክርስቶስን ወንጌለ መንግሥት እንዲሁም በነፍስም በሥጋም ጥቅም ያሰጠናል በማለት ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኛ ቦታ ሕንጻ በመግዛት የራስ ለማድረግ መሥዋዕትነት ተከፈለ። አረጋውያኑ ያጠራቀሙትን ገንዘብ በመስጠት ፤ ሶሻል የሚሰጠውን እየቆጠቡ ፤ ደመወዝተኛው ቤተ ሰቡን ጸም አሳድሮ በአጥፍ እየከፈሉ ፤ አንድ ሺ ለአንድ በተባለው የገንዘብ ማውጣት ዘዴ ሁሉም አወጣ።

የሕንጻ ኮሚቴዎቹም በችሎታቸው በሞያቸው (አርክቴክት ፣ ኤሌክትሪካል ኢንጂነር ፣ ሰርቪየር ሌሎችም...) ወይዛዝርቱ በበጋ ፀሐይ ፣ በክረምት ብርድ ላይ ቆመው ዳቦና ሻይ እንዲሁም እንጀራ ፣ ዳቦ ቆሎ በመሸጥ ፤ ነጠላቸውን ዘርግተው በመለመን ፤ በጽዋ ማኅበራት እንጀራና ወጥ አያቀረቡ በመሸጥ የተገዛ ሕንጻ ነው። ለዚህ ሕንጻ አደራ ጠባቂ ተደረገለት። ሆኖም ግን አደራ የተጣለባቸው ሰዎች አደራቸውን ዘነጉ ወይም አልተወጡም።

በዐቢይ ጾም መግቢያ መጋቢት ፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም. ጀምሮ በማን አለብኝነት ቤተ ክርስቲያኑ ዘጉ ፤ አዘጉ። ቅዱስ ጴጥሮስ “ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ“ (፭ ፣፫) የሚለውን ቃል በመዘንጋት ትንሹን ነገር ትልቅ በማድረግ የበጎቹን ቤት ዘጉ። ይህም ስለሆነ ከብርድና ከውርጭ እንዲሁም ከበጋው ፀሐይ ቃጠሎ ሲባል ምእመናኑ ጸሎት ማድረጊያ ድንኳን ገዛ። በድንኳኑ ውስጥ ጸሎት ማድረጉን ቀጠለ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የተዘጋውን ቤተ ክርስቲያን ታሕሣሥ ፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. ልንከፍት ነው ብለው ቅስቀሳ አደረጉ። የቻሪቲ ኮሚሽን ሰለም አውርዳችሁ ቤተ ክርስቲያኑን ክፈቱ አለ። ካህናቱና ምእመናኑ ሰለም ወርዶ ቢከፈት ይሻላል ፤ ከጸሎት በፊት የልብ ንጽሕና ይቅደም። መጸለይ የሚቻለው ልብን ንጹሕ አድርጎ መሆን ያስፈልጋል ተባለ። ነገር ግን “ድልን ተቀዳጀን” በሚል መንፈስ መንጋውን ለመስማት አልተፈለገም። መፍትሄው ይቅርታ ጠይቀው ፣ ሰለም አውርደው ፣ በፍቅር መክፈት ሲገባ ይህ አልተደረገም።
ጥያቄው

> ጉዳያችንን በውጭ ጨርሰን ፤ ተወቃቅሰን እንግባ በማለት መልእክት ተላልፎ ነበር። “ጎረቤት አንኳን ሲጣላ ቡና ለመጠጣት ታርቆ ነው” እንኳን ሥጋውንና ደሙን ለመቀበልና ለማቀበል አሉ።

የሚሰማ ግን አልነበረም። እሑድ ታሕሣሥ ፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. ጠዋት ፖሊስም ሕዝበ ክርስቲያኑም በቤተ ክርስቲያን ደረሱ። በቁጥር ምናልባት ወደ 15 የሚደርሱ ቦዲ ጋርዶች ነበሩ። አምስት መኪና ፖሊስ ዋናዎቹ የፖሊስ ኮማንዶዎች ለጸጥታ ሲባል መጡ። ጉዳዩ በሁሉም ልቡና ከፍተኛ ሐዘን እና ብስጭት አሳደረ።

ሆኖም ግን ምእመናኑ ዋናው ቤተ ክርስቲያን የጦርነት አውድማ ከሚሆን ወደውስጥ አንገባም በማለት ወደ 300 የሚደርስ ሕዝበ ክርስቲያን ዐረጋውያን ሽማግሌዎች ፣ ጎልማሶች ፣ ወጣቶች ፣ ሕጻናት በውጭ ቅጥረ ግቢ ውስጥ ቆመው ጸሎታቸውን አደረሱ። እነዚህም ቤተ ክርስቲያኒቷን ከ20 እስከ 40 ዓመት ያገለገሉ መሥራች ምእመናን እና ካህናት ነበሩ። ከፍተኛ ለቅሶ ተለቀሰ ፤ ወንዱም ሴቱም ሁሉም ዓይኑ ቀልቶ በአንባ ተሞልቶ ፤ ሲቃ እየተናነቀው ነበር።

> “እግዚአብሔር የሥራቸውን ይስጣቸው! የሰው እንባ እንዲህ ቀልድ ከሆነ እግዚአብሔር የለህማ! ማርያም እውነት የለሽማ! የሚሉት የእናቶች ለቅሶ ነበር!። ሲቃ እየተናነቃቸው ፤ እዬዬ በማለት አለቀሱ! በከፍተኛ ምሬት እንባቸውን ወደ ላይ ረጩ!” በድንኳን ጸሎቱ ቀጠለ።

ሆድ የባሰው ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰለት ምእመን በራሳቸው ቤት (በአባታቸው ቤት) ባይታወር ሆነው ከብርድ የተጠለሉበት ድንኳን

ምእመኑ ወደ ውስጥ ያልገባበት ምክንያት ከአለፈው ልምድ በመነሳት የሚያስከትለውን በመገንዘብ ነበር። ከወገኖቻችን ጋር ጸብ ፣ ረብሻ አንዳይፈጠር ፤ ግጭቱ ሲነሳ በቪድዮ ተቀርጾ አመጸኞቹ ያሰኙናል በሚል ነበር። ቤተ ክርስቲያን ከፍተናል ተባለ ነገር ግን የክርስቶስ መንጋ ተገፋ። ሰውን የሚያሸንፈው ፍቅር ነው። “ውሃን ምን ያስጨኸዋል ድንጋይ” እንደሚባለው ሰው ብሶቱን ያለምንም ምክንያት አያሰማም። ካገሩ ፣ ከቤተ ክርስቲያኑ የሁለት አገር ስደተኛ መሆኑን እየተሰማው ሆድ ብሶታል ፣ አስለቅሶታል ፣ አበሳጭቶታል...ሌላም።

ሆድ የባሰው ፤ የከፋው በሽ የሚቆጠረው የለንደን ምእመናን ዳኝነት ከበጎቹ ጠባቂዎች ስላላገኘ ከእግዜር እየጠበቀ ነው። በእርግጥም በደልን አይቶ መፍትሔ የሚሰጥ ፈጣሪ አምላክ ብቻ ነው።

ቤተ ክርስቲያኑ ከተዘጋ በኋላ በዐረፍተ ሞት የተለዩ ወደ ሰባት የሚደርሱ ምእመናን ወገኖች ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎ አልተሸኙበትም። ምክንያቱ ሆድ ስለሻከረ! የይቅርታ መንገድ ስላልተከፈተ! ነው።

የድንኳኑ ታሪክ በጥቂቱ ይህን ይመስላል።

“መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል” በድንኳን ላይ ተለጠፈ።

ይህ ቃል ለሁሉም ፤ ለመልካም እረኞች ሁሉ የተሰጠ ቃል ፤ ትእዛዝም ነው። ራሱ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል እንዲህ በማለት አዟል።

> “እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ **ትእዛዜ** ይህች ናት። **ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ** (ስለበጎቹ ምእመናን) ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ (ዮሐ. ፲፭ ፣፲፫)።”

ይህ በድንኳኑ ላይ የተጻፈው ጽሑፍና እንዲሁም የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ የተጻፈበት ምክንያት ሰውን ለማጥፋት ወይም “የበጎቹን ጠባቂ” አጥፍቶ የክርስቶስን መንጋ ለመበተን ስለተሞከረ። በምእመናኖች ፊት ኃጢአት ለማድረግ የሞከሩትና ያነበቡትን ዓለም እንዲያየው በድረ-ገጽም ጭምር በመውጣቱ። የከፋው! ሆደ የባሰው! “በጎቼን ጠብቅ” ተብለው በታዘዙት በደል የደረሰባቸው ምእመናን ጽፈው ለጠፉ። ማንም ሰው ጥቃትን አይወድም። “ለአቤቱታ የለው ይሉኝታ!” እንደሚባለው የተበደለ ሕዝብ ፤ ሆድ የባሰው የተገፋ ሕዝብ ዘወትር አቤቱታውን ከማሰማት አይመለስም። መፍትሄ ከመሪዎች ይፈልጋል።



ማጠቃለያ

መልካም እረኛ **ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል**” የሚለው ለመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ለሐዋርያቱ እና ለአማንያኑ የተነገረው ዛሬም ቃሉ “በጎቼን ጠብቅ” ለተባሉት ሁሉ ይሠራል። ለዚህም ቅዱስ ጴጥሮስ ምሳሌ ሆኖልን “በጎቼን ጠብቅ” እንደ ተባለ ፤ በርሱ አማካኝነት ካህናት በጎችን የመጠበቅ አደራነት ተሰጥቷቸዋል።

ዛሬም “ትወደኛለህ ወይ? እያለ ይጠይቃል!”

> መልሳችን አዎ አፈቅርሃለሁ! ከሆነ ፤ “በጎቼን ጠብቁ!” ይላል። ስለዚህ ለምንድነው የክርስቶስ መንጋዎቹ ላይ ጨካኝና ክፉዎች የሚኮነው?። ለራስ ክብር ሲባል መንጋው ላይ በር የተዘጋው ሌላም...።
>
> በሺ የሚቆጠር ምእመናንን ማሳዘን ማለት ፤ ጌታ ትወደኛለህን? ብሎ ሲጠይቅ አልወድህም! እንደ ማለት ይቆጠራል።

ለዚህ ሁሉ ለእንደን ምእመናን መሰቃየት ዋናው ነገር ጭካኔነት ነው። በክርስቶስ መንጋዎቹ ላይ በማያስፈልግ መንገድ ፤ በፈሊጥ ሳይሆን በኃይል በመጠቀም ፤ ነገርን ባጭር መቅጨት ሲገባ ፤ የቤተ ክርስቲያን በር ዘግቶ ኢትዮጵያ ድረስ በመሄድ በጋዜጣ ፖለቲከኞች በማለት በማስወጣት ፣ እንደገና በሌላ ክፍል “በጎቼን” ለመጉዳት ፤ ይበልጥ ደግሞ “አብረው የኖሩትን ወዳጅን በመክዳት” ለማስወገዝ በመሞከሩ ነው።

አሁንም ቢሆን መልካም የሆኑት እረኞች (የበጎች ጠባቂዎች) ሁሉ በምድር አይደለም ለዘላለማዊው በሆነው በምድራዊ ሳይሆን በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ስማቸው እንደሚጻፍላቸው የታመነ ነው። ወገንን የሚጠቅም ሥራ ለሥራ ስሙ ለዘለዓለም በፈጣሪ ዘንድ ይጻፍለታል።

በቤተ ክርስቲያን ላይ ቀልዱ እና ዝርጠጣው ቀርቶ። በቅዱስ ጴጥሮስ አማካይነት “ግልገሎቼን! ጠቦቶቼን! በጎቼን! ጠብቁ“ (የሐ. ፳፩ ፣፲፯) በማለት እንደታዘዘው ቢገቢር ማሳየቱ መልካም ነው። *እንዲሁም ሰማያዊ አባቱ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ አይፈቅድም* (ማቴ. ፲፰ ፣፲፬) በማለት ጌታ እንዳስተማረው “በጎቼን ጠብቁ” ብሎ በአደራ የሰጠ ስለሆነ ማንም ሊጠፋ አይፈለግም። ለሁሉም ይቅር ማለት እና በፍቅር መኖር ይበልጣል።

መዝሙር = ኖላዊ ትጉህ ዘኢትነውም (2)
ማኅበረነ ማኅበረነ ዕቀብ በሰላም (2)

ትርጉም = የማትተኛ ትጉህ እረኛ ሆይ!
ማኅበራችንን በሰላም ጠብቅ!።

ጸሎት = የሰላም ንጉሥ ሆይ አንድነትን ስጠን ፤ ሁሉን ሰጥተህናልና አማዚአብሔር ሆይ ገንዘብ አድርገን ፤ ጸጋህን ም ስጠን። ካንተ በቀር ሌላ የምናውቀው የለም። ቅዱስ ስምህን እንጠራለን። በሰማይ ያለ ሠላምህን አንተ በሁላችን ሰውነት አሳድር። በዚህ ዓለም አናኑራችንን በሠላም አቅናልን። አሜን!!

“ከመነቃቀፍ ይሻላል መተቃቀፍ” ፤ መለያየት ልብን ያደክማል። ኃይል የምንሆነው ቅዱስ ዳዊት “እነሆ ወን ድሞች ተባብረው ሚኖሩ መልካም ነው” (መዝ. ፻፴፪ (፻፴፫)) እንዳለው የሚያምርብን ተፋቅረን ተከባብረን ልጆቻችንን እናስተምር ፣ ጎልማሶቻችንን እንዳር ፣ ሽማግሌዎቻችንን እንጠር ፤ በሰላም በስደት ባለንበት አገር እንኑር።

የሰላም የፍቅር ባለቤት አማዚአብሔር ይርዳን ፤ አሜን!
የፍቅር ፣ የሰላም እናት አመቤታችን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም በበረከቷ አትለየን ፤ አሜን!
መልአከ ብርሃን ቀሲስ ብርሃኑ ብሥራት

ዋቢ መጻሐፍት

- መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፲፱፻፹፪ ዓ.ም.
- ወንጌል ቅዱስ ፤ ንባብና ትርጓሜ ፤ በርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.
- ምክረ ሥላሴ ገ.አማኑኤል {ዶክተር} ፤ *የሰብከተ ወንጌል ምአላድ* ፤ አዲስ አበባ ፪ሺ፫ ዓ.ም.
- ቡሩክ ገብረ ሊባኖስ ተስፋዬ ፤ *የሰው ያለህ* ፤ አውስትራሊያ ሜልበርን ፪ሺ፭ ዓ.ም.
- **Murphy. *The New Jerome Biblical Commentary*, Bath Press, Avon 1990**
- **William, R. *The International Bible Commentary*, Minnesota Liturgical Press. 1998**